# የዮሴፍ ሕይወት (16)

ዮሴፍ ያዕቆብ ከሚወዳትና የመጀመሪያውን ሰባት ዓመታት እርሷን ለማግባት ሲል ለአባቷ ለላባ ከተገዛላት ከራሄል የወለደው ልጁ ነበረ:: ዘፍ 30:22-24

ያዕቆብ ዮሴፍን ከሌሎቹ ልጆቹ አብልጦ እንደሚወደው ዘፍ 37:3 ላይ ግልጽ ብሎ የሰፈር እውነት ነው:: ይህ በአባቱ በተለየ መንገድ የመወደዱ ሁኔታ በወንድሞቹ ዘንድ ደግሞ እጅግ የተጠላ እንዲሆን አድርጎታል::

ዮሴፍ በአባቱ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሄርም ዘንድ ሞገስ እንዳገኘ በተለይም በህይወቱ በስተኋለኛው ክፍል ግልጽ ሆኖ ይታያል:: ይህ ሰው በተለያዩ ጊዜያት ህልምን ያለመና ህልሞቹም ጠብ ሳይሉ ፍጻሜን ያገኙ እንደሆነ ይታወቃል::

ይህ ወጣት ዮሴፍ ያያቸውን ህልሞች ለወንድሞቹና ለቤተሰቦቹ አንድም ሳይቀር ዘክዝኮ በመንገሩ ምክንያት የወንድሞቹ ጥላቻ ስላየለባቸው ዮሴፍን ለማስወገድ ውሳኔ አደረጉ:: በዚህም ምክንያት እርሱን መግደል የሚያስገኘው ጥቅም ስለሌል ቢሸጥ የሚሻል እንደሆነ ስላመኑበት ወደ ግብጽ በባርነት በመሸጥ ህልሙ ፍጻሜ ወደ ሚያገኝበትና እግዚአብሄር ለራሱ የሚሆነውን ህዝብ ወደሚያስገኝበት የተወሰደው በዚያ መንገድ ነበረ::

የዮሴፍ ህልም ፍጻሜ ከማግኘቱና በግብጽ ምድር ከፍተውን ስፍራ ከመያዙ አስቀድሞ ያለፈባቸው መንገዶች አስቸጋሪና ፈታኝ ሁኔታዎች እንደነባሩ የዘፍጥረትን መጽሐፍ ያነበበ ሁሉ ለመረዳትና ለማየት አያዳግተውም::

ዮሴፍ ከፍ ከፍ የማለትን ህልም ያልም እንጂ በመጽሃፍ ቅዱሳችን ውስጥ የተዘረዘሩትን ለክብር ያበቁትን አበይት ሁኔታዎች ከታሪኩ ውስጥ ለማየት ይቻላል:: ከእነዚህም መሃል ጥቂቶቹን ለማየት ያህል፡-

- እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ እንደነበረ የሚያስመሰክር ህይወት ነበረው:: 39:2-3
- ስራውን በታማኝነት የሚሰራ ሰው ነበረ:: 39:5-6
- ለፈተና እንቢ የሚል ጠንካራ ባህርይ ነበረው:: 39:7-9
- ክብርን ለእግዚአብሄር መስጠት አይከብደውም:: 41:16

ስለ ዮሴፍ ህይወት ህይወት ያጠኑ ሰዎች ሁሉ በብሉይ ኪዳን ከሚታዩት ከማናቸውም ሰዎች ህይወት ይልቅ በርሱ ህይወት የሚታዩት አብዛኛዎቹ ባህርዮቹ ከርስቶስ ባህርይ ጋራ ተመሳሳይነት እንዳላቸው ያምናሉ:: ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል:

- ወንድሞቹን ይቅር ማለቱ 45:15
- ክፉን በመልካም ማሸነፍ 50:19-21
- ለፈተና እንቢ አሻፈረኝ በማለቱ 39:7-13
- ለተራበ ሁሉ እንጀራ የሚገኘው ከእርሱ ብቻ መሆኑና ወዘተ...

መጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪካቸው ከሰፈረላቸው ማናቸውም የእግዚአብሄር ሰዎች ማንም የዮሴፍን ያህል ሰፊ ቦታ ይዞ ታሪኩ የሰፈረለት ሰው የለም:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ሰፊ ስፍራ ለሰጠው ሰው እኛም ልባችንን በማስፋት ከመንፈስ ቅዱስ ለመማር በተዘጋጀ ልብና በጸሎት ወደቃሉ እንቅረብ::

# ጥናት አንድ (ዘፍ 37:1-30)

የጥናት ዓላማ፡- በልባችን መልካም ሃሳብ መያዝ ብቻ በቂ እንደማይሆንና ዋጋ የሚያስከፍለንም ቢሆን በጊዜው እውነት ብለን ያመንበትን ሃሳብ ገልጸን መናገር አስፈላጊ መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ: «ሮቤል ይህን ያለው ህይወቱን ከእጃቸው አትርፎ ወደ አባቱ ሊመልሰው አስቦ ነበር፡፡» ዘፍ 47:22

1. ዮሴፍ በወንድሞቹ የተጠላው ለምን ነበረ?
2. የዮሴፍን ሁለት ህልሞችና ትርጉማቸው ምን እንደሆነ አብራርተህ ተናገር፡፡
3. የዮሴፍ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይሰፍርልን የእስራኤልን ህዝብ አመጣጥ ለመረዳት አስቸጋሪ የሚሆነው ለምንድነው?
4. ዮሴፍ በወንድሞቹ እንዲጠላ ያዕቆብ ያደረገው አስተዋጽዖ አለ ትላለህ ወይ? ከሆነስ ይህ እርሱ ያደረገው አስተዋጽዖ ምን እንደነበረ ተናገር፡፡
5. የወንድሞቹ ጥላቻ ከእለት እለት እያደገ መሄዱን የሚያመለክቱትን ሃሳቦች ከክፍሉ በማውጣት አስረዳ፡፡ በውስጣቸው የሞላውን ጥላቻ ለመወጣትስ እስከ ምን ድረስ ለመሄድ ፈቃደኛ እነደነበሩ ታያለህ?
6. ኤርምያስ 17:9 የሚናገረውን ሃሳብ በዚህ ክፍል ካነበብነው ታሪክ ጋራ እንዴት ልታገናዝበው ትችላለህ?
7. «...ሰው የሚዘራውን ያንኑ ያጭዳል፡፡» ገላ 6:7 የሚለው ጥቅስ እንዴት ነው በዮሴፍ ወንድሞች ህይወት ሲፈፀም የምታየው? በአባታቸው በያዕቆብ ህይወትስ በተለይ በታረደ ፍየል መታለሉ ይህንን ቃል ተፈጻሚ ያደረገው በምን መንገድ ነው?
8. ቁ 21-22 እና 26 ስናነብ ሮቤልና ይሁዳ በዮሴፍ ላይ በተሸረበው ሴራ ሙሉ ለሙሉ አልተስማሙም፡፡ ታዲያ በቀጥታ ለአባቱ እንነግራለን አይሸጥም አይገደልም አላሉም? በእነዚህ ሁለት ወንድሞቹ ምን ስህተት ታያለህ?
9. ከነዚህ ሁለት ወንድማማቾች ስህተት እያንዳንዳችሁ ምን እንደተማራችሁ ከወገኖች ጋራ እርስ በእርሳችሁ ተከፋፈሉ፡፡

# ጥናት ሁለት (ዘፍ 39:1-23)

የጥናት ዓላማ: በደስታቸው ጊዜ እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ጋራ የሚገኘውን ያህል በመከራ በሚያልፉባቸውም ጊዜያት አበሯቸው እንደሚሆን ለማሳየት።

የምናሰላስለው ጥቅስ: «ይሁን እንጂ ዮሴፍ እዚያ እስር ቤት ባለበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ ነበር።» ዘፍጥረት 39:21

1. በዘፍ 39:1-6 እግዚአብሄር በዮሴፍ ህይወት ሲሰራ የምታያቸውን ነገሮች በሙሉ በቅደም ተከተል ዘርዝር። ይህንን ሰው ለዚህ ሁሉ እድገት ያበቃው ዋነኛ ምክንያት ምን ነበረ?
2. ጲጥፋራ ከዮሴፍ ህይወት የተመለከተው ዋነኛ ነገር ምን ነበረ? አማኝ ከአሰሪው ሞገስ ለማግኘት ማድረግ ስለሚገባው ነገር ይህ ክፍል ምን ያስተምረዋል?
3. ቁ 7-12 ላይ የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን አብሯት እንዲተኛ ስትጠየቀው እንቢ ለማለት የሰጣት ምክንያት ምን ነበረ?
4. በዚሁ ክፍል ውስጥ ዮሴፍ ንግግሩን ሲጀምር ጌታው እምነት እንደጣለበትና እርሱን ማሳዘን ስለማይፈልግ አብሯት መተኛት እንዳልፈለገ ይነግራታል። ታዲያ በመጨረሻ ነገሩን ከእግዚአብሄር ጋራ ያያያዘበት ምክንያት ለምንድነው?
5. ቁጥር 13-18ትን በማንበብ ሴቲቱ የምትፈልገውን ስላላገኘች ተበሳጭታ ያቀነባበረችውን የውሸት አይነቶች አንድ በአንድ ዘርዝር።
6. ባልየውን በሚያሳምን መንገድ ሁኔታውን አቅርባ አሳምናው ሊሆን ይችላል። ይህ ታሪክ ከአንዱ አቅጣጫ ብቻ ሰምቶ መፍረድ ስለሚያስከትለው ሁኔታ ምን ትማራለህ?
7. 39:2-4 ትንና 39:21-23 ትን በማነጻጸር ተናገር።
8. ጥያቄ ቁጥር ሰባትን በመመርኮዝ፤ ዮሴፍ በጲጥፊራ ቤት በድሎት ሳለና ኋላም በእስር ቤት ሳለ እግዚአብሄር ጋራ የነበረው ግንኙነት ምን ይመስል ነበር? በድሎትም ሆነ በእስር የእግዚአብሔር ከእርሱ ጋራ መሆን ምን ይናገርሃል?
9. 1ኛ ጴጥ 4:14-16 ትን ዮሴፍ ከሚገኝበት ሁኔታ ጋራ በማገናዘብ ሃሳብህን ሰንዝር። ቢያስከፍልም እንኳን በእግዚአብሄርን ላለመበደል ውሳኔ አድርግ።

# ጥናት ሶስት (ዘፍ 40:1-23)

*የጥናት ዓላማ: የእግዚአብሄር አገልጋይ ሰዎች ሊሰሙ የሚፈልጉትን ብቻ ሳይሆን መስማት የማይወዱተንም እውነት በታማኝነት መናገር እንደሚገባው ለምማር::*
*የምናሰላስለው ጥቅስ: «...ፈርዖን ከእስር በቤት ያወጣሃል፤ በእንጨትም ላይ ይሰቅልሃል፤ ወፎችም ሥጋህን ይበሉታል::»* **ዘፍጥረት 40:19**

1. በመጠጥ አሳላፊውና በእንጀራ ቤቱ ሃላፊ ህይወት ላይ የተከሰተውን ሁኔታ በቅደም ተከተል ለመዘርዘር ሞክር:: (ቁ 1-4)
2. በቁ 5-8 ላይ እነዚህን ሁለት የንጉስ እስረኞች ልባቸውን በሃዘን የመታው ነገር ምን ነበረ? ከዮሴፍ መልስ አሰጣጥ ምን ትማራለህ?
3. ለመጠጥ አሳላፊው እግዚአብሄር ከሰጠው ከህልሙ ፍቺ ውጪ ዮሴፍ ከራሱ የተናገረው ነገር ምንድነው?
4. ዮሴፍ እግዚአብሄር ከሰጠው መልዕክት ውጭ እንዲያስተላልፍ የተገፋበት ምክንያት ምንድነው? እኛ ራሳችን በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውሰጥ ልንገባ የምንችልባቸውን አንዳንድ ሁኔታዎች ተናገር:: (ቁ 9-15)
5. በመጠጥ አሳላፊውና በእንጀራ ቤቱ ሃላፊ ሕልሞች የሚመሳሰሉበትን ነጥቦች ተናገር:: የህልሞቹን ፍችና ትርጉማቸውን አነጻጽር:: (ቁ 9-13 እና 16-19)
6. ለዮሴፍ ከሁለቱ ሰዎች ለማንኛቸው ፍቺውን ለመናገር የሚከብደው ይመስልሃል? ለምን ይህንን ለማለት ቻልክ?
7. ከዮሴፍ የምናየው መልካሙንም ክፉውንም ዜና ሳያመቻምች መናገሩ በምክርም ሆነ በትምህርት መልክ ስለምናስተላልፋቸው ነገሮች ምን ያስተምረናል?
8. የመጠጥ አሳላፊው በችግሩ ጊዜ ዮሴፍን መፈለጉና ሲሳካለት መርሳቱ ስለ ሰው ልጅ ባህርይ ምን ያሳየናል?
9. መልካምም ሆነ ክፉ ሆኖ ሰዎች የሚያዩትን ነገር እግዚአብሄር ያለው ከሆነ ለመናገር ምን ያህል ልብህ የጨከነ ነው? እሱ ያከበሩትን ያከብራልና በርታበት::

# <u>ጥናት አራት (ዘፍ 41:1-24)</u>

**የጥናት ዓላማ፡ የቱንም ያህል ሰዎች ቢረሱን እግዚአብሔር ጊዜውን ጠብቆ እንደሚያስበን ለመማርና ለመበረታታት፡፡**

**የምናሰላስለው ጥቅስ፡ «ፈርዖን ዮሴፍን እንዲያመጡት ተዕዛዝ ሰጠ፤ከእስር ቤትም በጥድፊያ ይዘውት መጡ፡፡» ዘፍጥረት 41:14**

1. በዘፍ 41:1-7 መስረት ፈርዖንን ከእንቅልፉ የቀሰቀሰው ነገር ምን ነበር? ያየው ህልም ምን እንደነበረና ጊዜው መቼ እንደነበረ በዝርዝር ተናገር፡፡
2. የመጠጥ ቤት ሃላፊው ለፈርዖን ያደረገው ኑዛዜ ምን ነበረ? ለምንድነው ይህ ሰው የሕይወቱን አቅጣጫ የነገረውን ሰው ያህል ሊረሳ የቻለው? (ቁጥር 8-13)
3. በቁ 14-16 በዮሴፍና በፈርዖን መካከል የተካሄደውን ውይይት ተናገር፡፡ ዮሴፍ እንዲመጣ ስለተደረገበት ሁኔታ ይህ ክፍል ምን ይነግረናል?
4. ቁ 14 ላይ «...በጥድፊያ ይዘውት መጡ» የሚለው ሃሳብ ስለ እግዚአብሄር አሰራር የሚያስተምረን እውነት ምንድነው?
5. ዮሴፍ ህልምን የመተርጎም ስጦታ እያለው ለምንድነው የመተርጎም ችሎታ የለኝም ብሎ የተናገረው? ቁ 16
6. የፈርዖንና የዮሴፍ ህልም የሚመሳሰልበት አንድ ነገር ምን ነበረ? ዮሴፍ ሁለት ተመሳሳይ ህልሞች አልሞ እስከዛሬ አለመፈጸሙ እንዴት ተስፋ አላስቆረጠውም?
7. ዮሴፍ ያለመው የራሱ ህልም ገና ተፈጸሞ ሳያይ የፈረዖንን ህልም ለመፍታት በድፍረት ለመቆም ያስቻለው ምክንያት ምንድነው?
8. ፈርዖን ለዮሴፍ ያየውን ህልም እነዳለ በቁ 17-24 ውስጥ ይነግረዋል፡፡ ታዲያ ለምንድነው ፈርዖን አስማተኞቹ ሊፈቱት እንዳልቻሉ ለዮሴፍ መናገር ያስፈለገው?
9. «የሰራሁት በደል ዛሬ ታወሰኝ፡፡» 41:9 የዚህን ሰው እስከ ዛሬ የረሳውን ነገር ያስታወሰው ማን ነው? ለምን ይህንን ልትል ቻልክ? «...በጥድፊያ ይዘውት መጡ» ከሚለው ጋራ አጣምረን ስናየው ምን መማር እንችላለን?
10. በዚህ ክፍል የተማርነው እውነት በራሳችን ህይወትና ሁኔታዎች ላይ እንዴት ተፈጻሚነት ይኖረዋል?

# ጥናት አምስት (ዘፍ 41:25-56)

የጥናት ዓላማ: አማኝ በእግዚአበሄር ላይ ሙሉ ለሙሉ በመደገፍ የአጭርም ሆነ የረጅም ጊዜ እቅድ መንደፍ እንደሚችል ለመማር::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «እቅዱንም ፈርዖንና ሹማምንቱ ሁሉ መልካም ሆኖ አገኙት:: ዘፍጥረት 41:37»

1. ቁ 25-32 ትን በማንበብ የፈርዖንን የህልም ፍቺ በራስህ ቃላት ተናገር::
2. በረሃቡና በጥጋቡ ዘመን መደረግ ስላለባቸው ነገሮች የዮሴፍ ምክር ምን ነበረ? የዮሴፍን ዕቅድና ፕላን ሲሰማ የፈርዖን ምላሽ ምን እንደነበረ ግለጽ:: ቁ 33-40
3. ፈርዖን ዮሴፍን የእግዚአብሄር መንፈስ ያለበት ሰው በማለት ሊናገር ያስቻሉትን ምክንያቶች ተናገር:: ዛሬ በስራህ ወይም በትምህርትህ ስፍራ ሰዎች ስላንተ የሚናገሩት ምስክርነት ምን ይመስላል?
4. ይህ ታሪክ በተፈጸመበት ወቅት ዮሴፍ በግብጽ ምድር ስንት ዓመቱ ነበረ? እነዚህን ዓመታት ያሳለፈው የት ነበረ? ቁ 47 ትን ተመልከት::
5. ሰዎች በህይወታችን የሚያደርሱብንን ጉዳት መርሳትና ፍሬአማነት ሊገናኝ የሚችለው በምን መንገድ ነው? ጉዳታቸውን ሊተውና ሊረሱ ለማይፈልጉ ሰዎች ይህ ክፍል የሚሰጠው ትምህርት ምንድነው?
6. እግዚአብሄር ለዮሴፍ በእስራኤል ነገድ ውስጥ ሁለት እጥፍ ርስት የሰጠው በምን መንገድ ነው? ዘፍ 41:50-52፤ 1ኛ ዜና 5:1-2
7. በባዕድ ምድር በመከራ መሃል ዮሴፍ ፍሬአማ የሆነበት ምክንያት ምን ነበረ?
8. ለልጆቹ ያወጣላቸውን ስም በመመልከት ዮሴፍ ስለ እግዚአብሄር ስላለው መረዳት ምን እንማራለን? ዘፍ 41:50-52
9. ብዙ ጊዜ ዮሴፍ ለኢየሱስ ምሳሌ እንደሆነ በብዙ መንገድ ይታያል:: በቁጥር 55 እንደምናነበው ፈርዖን እንኳን ህዝቡን እንጀራ ሲጠይቁት የሚልከው ወደ ዮሴፍ ነበረ:: ይህ ሁኔታ በእኛ ህይወት የሚኖረው መንፈሳዊ ትርጉም ምንድነው?
10. ቁ 33-36 የነደፈውን እቅዱን በቁ 47-49 በስራ ተፈጻሚ ማድረጉ ስለ ዮሴፍ ምን ይነግረናል? በዚህስ መሰረት እቅድንና አፈጻጸምን በተመለከተ ለራስህ ምን ትማራለህ? እቅድ ታወጣለህ ወይ? በእቅድህስ ውስጥ እግዚአብሄር አለበት ወይ?

# ጥናት ስድስት (ዘፍ 42:1-38)

የጥናት ዓላማ:- ክፉን በመልካም ማሸነፍ በቃል በአንደበቱ ብቻ ሳይሆን በተግባር ያስመሰከረ ሰው እንዳለ ከዮሴፍ ሕይወት በተጨባጭ ለመማር::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «በስልቻዎቻቸው እህል እንዲሞሉላቸው ብሩንም በእያንዳንዱ ሰው ስልቻ ውስጥ መልሰው እንዲያስቀምጡና ለጉዟቸው ስንቅ እንዲያሲዟቸው ዮሴፍ ትዕዛዝ ሰጠ::»

1. «...እህል ለመሸመት ወደ ግብጽ ወረዱ::» እነዚህ አስር ሰዎች ወደ ግብጽ ጉዟቸው ወደ አእምሮአቸው ሊመጣ የሚችለው ትዝታ ምንድነው?
2. ቁ 6 «...ወደ ምድር ለጥ ብለው እጅ ነሡት::» ቁ 8 «...ያየው ህልም ትዝ አለውና፣» ይህ ሁኔታ ለዮሴፍም ሆነ ለእኛ የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?
3. የወንድሞቹ ወድቆ ለዮሴፍ መስገድ እግዚአብሄር ያሳየውን ህልም ለመፈጸም የወሰደበት ጊዜ ስንት ዓመታት ነበረ? እግዚአብሄር የተናገረውን ቃል ጨብጠህ ሃያ ዐመት ለመጓዝ በራስህ ህይወት ምን ዝግጁነት ታያለህ?
4. እንዴት ከአስሩ አንዱ እንኳን ዮሴፍን ሊያውቀው አልቻለም? ሞቷል ብለው ስለደመደሙ (42:22) ፤ እዚህ ደረጃ ይደርሳል ብለው ስላልጠረጠሩ...ወዘተ
5. ቁ 11 እና 31 ስትመለከት እነዚህ ሰዎች ስለራሳቸው ያላቸው ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? እነዚህ ሰዎች የሚሉትን አለመሆናቸውን በምን መንገድ ታረጋግጣለህ?
6. ቁ 21-23 ላይ ወንድማማቾቹ ከሚነጋገሩት ንግግር የምትረዳው ነገር ምንድነው? «ደሙ ከእጃችን ይፈለጋል የሚለው አባባል ምን ይነግረናል?
7. «አንዱ የለም» ቁ 13 ና 32 በማለት በነዚህ ሁለት ቃላት የዮሴፍን ነገር ለመዝጋት መሞከራቸው ለምንድነው? በቁ 28 የጠየቁት ጥያቄ ለምን ወደ ንስሃ አላመጣቸውም?
8. 42:29-34 ወንድማማቾቹ ለአባታቸው ያቀረቡት ሪፖርት ምን ነበረ? ቁ 21-23 ስንመለከት ስህተታቸውን አምነዋል ለአባታቸው ሪፖርት ሲያቀርቡ ወደንስሃ ግን አልመጡም::
9. ቁ 23 ላይ «...እንደሚሰማቸው አላወቁም ነበር::» ይህ ውይይት በዮሴፍ አዕምሮ የረሳውን ክፉ ነገር እንደሚያስታውሰው አያጠራጥርም:: የዮሴፍ ምላሽ ቁ 25 ላይ የምናነበው መሆኑ ምን ያስተምረናል? ሮሜ 12:19-21 ትን በሚገባ ለመረዳት ይህ ክፍል ምን ያህል ረድቶሃል?

# <u>ጥናት ሰባት (ዘፍ 43:1-34)</u>

የጥናት ዓላማ፡- በሃጥያታችን ለመስቀል ሞት ያበቃነው ኢየሱስ አንዳች እንዳልበደልነው ሁሉን ይቅር በማለት አንድ ቀን ከእርሱ ጋራ በማዕድ እንደሚያስቀምጠን ለማሳሰብ፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ «...ዛሬ ቀትር ላይ አብረውኝ ስለሚበሉ ፍሪዳ ተጥሎ ምሳ ይዘጋጅ አለው፡፡» ዘፍ 43:16

1. ዘፍ 43:1-14 ባለው ክፍል በያዕቆብና በልጆቹ መካከል የተካሄደውን ውይይት በራስህ ቋንቋ ተናገር፡፡
2. ቁ 1-2 ሲነበብ ያዕቆብና ልጆቹ ስለ ረሃቡ ክፋትና ርዝመት ገብቷቸዋል ወይ? ለምን ይህንን ልትል እንደቻልክ አስረዳ፡፡
3. ለምንድነው በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ደጋግመው «ያ ሰው...» በማለት ዮሴፍን የሚጠሩት? (ቁ 3፤ 5፤ 7፤ 13፤ 14) ይህ አባባል ዮሴፍን ከኢየሱስ ጋራ የሚያመሳስለው በምን መንገድ ነው? ዮሐ 19:5
4. በቁጥር 11 ላይ የዮሴፍ ወንድሞች ለዩሴፍ የወሰዱትን እጅ መንሻ እኛ ለእግዚአብሔር ልንሰጥ ከምንሞክረው ስጦታ ጋራ የሚነጻጸረው በምን መንገድ ነው?
5. ሉቃ 15:22-24 ትንና ዘፍ 43:16 ትን በማንበብ በሁለቱ ክፍሎች ውስጥ የምታያቸውን ሃሳቦች አነጻጽረህ ተናገር፡፡
6. ወንድማማቾቹ በቁ 17-18 ላይ ሲነጋገሩ የምንመለከተው ነገር ስለ ሃጥያት በአጠቃላይ የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?
7. ዮሴፍ እጅ መንሻ ሲቀርብለት በምላሹ እርሱ ያተኮረው በእነርሱ ደህንነት ላይ እንደነበረ እንመለከታለን፡፡ እግዚአብሄር ከእኛ ጋራ ስላለው ግንኙነት ከዚህ ክፍል ምን ታየለህ?
8. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚካሄደውን ሁኔታ ለሚመለከቱት ሰዎች ስለ ያዕቆብ ቤተሰብ የሚሰጠው ስዕል ምን ዓይነት ነው? ይህ ስዕል ይህንን ሊመስል የቻለበትስ ምክንያት ምንድነው?
9. የዮሴፍ ወንድሞች በተደረገላቸው ግብዣ የተሰማቸው ስሜት ምን ይመስል ነበረ? አንተስ በበጉ ራት ላይ እድምተኛ መሆንህ በውስጥህ የሚፈጥረው ስሜት አለ ወይ? ካለ ስሜትህን ተናገር፡፡

# ጥናት ስምንት (ዘፍ 44:1-34)

የጥናት ዓላማ:- እንደ ጌታ ልጆች ዋጋ የሚያስከፍለንም እንኳን ቢሆን የገባነውን ቃል ለመጠበቅ መትጋት እንደሚኖርብን ለመማር::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «ስለዚህ አሁን አገልጋይህ በልጁ ፈንታ የአንተ የጌታዬ ባሪያ ሆኜ ልቅር...» ዘፍ 44:33

1. በመጀመሪያዎቹ ቁጥሮች ላይ ዮሴፍ ለባሪያው የሰጠው ትዕዛዝ ምን ነበረ? ሎሌው ለተናገራቸው ክስ የወንድማማቾቹ ምላሽ ምን እንደነበረ ዘርዝር::
2. ከቁ 7-9 ላይ የዮሴፍ ወንድሞች ምላሻቸው ለምን ይመስልሃል በጣም በእርግጠኛነት የተሞላው?
3. በቁ 9 ላይ በእርግጠኛነት የተስማሙበት ነገር ለምንድነው የጽዋው መገኘት ልብሳቸውን እስኪቀዱ ድረስ ያሳዘናቸው? ቁ 13
4. በቁጥር 18 ላይ የምታየው የይሁዳ አለማመን ከመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ማንን እንደሚያስታውስህ ተናገር:: በዚህ ምዕራፍ በአጠቃላይ ይሁዳ ራሱን እንዴት አድርጎ ነው ሲያቀርብ ነው የሚታየው?
5. ዮሴፍን ወደሸጡበት ሃገር መሄዳቸው፣ ዮሴፍ ስላባታቸው መጠየቁ፣ ብንያምን አምጡ መባላቸው፣ ለሌሎች የማይደረግ ግብዣ መጋበዛቸው፣ ደጋግመው ለዮሴፍ መስገዳቸውና...ወዘተ ሰውየው ዮሴፍ ለመሆኑ ለምን ጥርጥር አልገባቸውም?
6. ስለ ይሁዳ ከዚህ ምንባብ ውጭ የምታውቃቸውን ነገሮች በመዘርዘር ተናገር:: በ43:16-34 የምታነበውን ቀድሞ ስለርሱ ከምታውቀው ጋራ በማነጻጸር ተናገር::
7. ቁ 32ትንና ቁ 33ትን ስታነብ በይሁዳ ህይወት ጎልቶ የሚታየው እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት ባህርይ ምንድነው? ይህ ድርጊት ከይሁዳ ነገድ በሆነው በኢየሱስ ህይወት ውስጥ በምን መንገድ እንደተገለጠ በማዛመድ ተናገር::
8. በይሁዳ ህይወት የታየው ዋጋን የሚያስከፍል ዓይነት ቃልን መጠበቅ ምን ያህል በህይወትህ ትለማመዳለህ? አንድን ነገር አደርጋለሁ ከማለትህ በፊት ምን ያህል አስቀድመህ ታስባለህ? መክብብ 5:5
9. ከክፍሉ የተማርከውና ልብህ ውስጥ የቀረ ነገር ካለ ለወገኖች አካፍል::

# ጥናት ዘጠኝ (ዘፍ 45:1-28)

የጥናት ዓላማ:- በጭንቀትና በመከራ ውስጥ ስናልፍ እግዚአብሄር በዚያ ውስጥ ሊያሳድገን ከዚያም አልፎ ለሌሎች በረከት ሊያደርገን እንደሆነ በማሰብ በእርሱ መተማመንን እንድንለማመድ ለማበረታታት፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ: «...ምክንያቱም እግዚአብሄር ህይወት ለማዳን ሲል ከእናንተ አስቀድሞ እኔን ወደዚህ ልኮኛል፡፡» ዘፍ 45:5

1. ዘፍ 45:1-28 በአንድነት ይነበብ፡፡ ዮሴፍ ራሱን ለወንድሞቹ በገለጠ ጊዜ የነበረውን ሰሜት በራስህ ቃል አስረዳ፡፡ ከምን የተነሳ ነው ዮሴፍ ስሜቱን ሊገታ እንዲቸገር የሆነው?
2. ለምንድነው የዮሴፍ ወንድሞች በቁ 3 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ መስጠት ያልቻሉት?
3. መደናገጣቸውን የተመለከተው ዮሴፍ በምን መንገድ ነው ወንድሞቹን ማጽናናት የቻለው?
4. ከቁጥር 4-8 ያለውን ስታነብ ዮሴፍ አንድ በጣም እርግጠኛ ሆኖ የሚናገረው ነገር ምንድነው? ምንድነው ይህ ሰው ይህንን ያህል እርግጠኛ እንዲሆን ያደረገው?
5. በቁ 3 እና በቁ 15 መሃል ምን ልዩነት ታያለህ? ይህ ዓይነት ልዩነት እንዲታይ ያደረገው ምክንያት ምንድነው ትላለህ?
6. ሮሜ 12:15 የሚያዘንን ትዕዛዝ ፈርዖንና ሹማምንቱ በስራ ላይ ያዋሉት እንዴት ነው?
7. በቁ 26 ላይ የሰጡት ሪፖርት ዮሴፍን ከሸጡት በኋላ ከሰጡት ሪፖርት የሚለየው እንዴት ነው? ይህ ወቅት ለወንድማማቾቹ ንስሃ ለመግባት ምን ያህል አመቺ ሆኖ ታየዋለህ? ንስሃ አለመግባታቸው ምን ያሳይሃል?
8. በዚህ ሁሉ ዮሴፍ ስላየው ህልምና ፍጻሜው አለማንሳቱ የሚያስተምርህ እውነት አለ ወይ? ካለስ ያ እውነት ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
9. የምታልፍበት አስቸጋሪ ሁኔታ ሲኖር ነገ ለሌላ ሰው በረከት የሚሆን ፍሬ እንዲፈራ እግዚአብሄር ያቀደው ሊሆን እንደሚችል አስበህ ታውቃለህ ወይ? ከዛሬ በኋላ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ስታልፍ የዮሴፍን አስተሳሰብ ለማዳበር ትጋ፡፡

# ጥናት አስር (ዘፍ 46:1-34)

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ሰው ለገዛ ቤተሰቦቹ የማሰብና የመጠንቀቅ ግዴታ እንዳለበት ለመማር::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «አንድ ሰው ዘመዶቹን፣ በተለይም የቅርብ ቤተሰቡን የማይረዳ ከሆነ ሃይማኖቱን የካደ፣ ከማያምንም ሰው ይልቅ የባሰ ክፉ ነው::» 1ኛ ጢሞ 5:8

1. ዘፍ 46:1-34 በአንድነት ይነበብ:: በቁ 1-7 የተካሄደውን ነገር በራስህ ቋንቋ ተናገር::
2. በቁ 1 ላይ ያዕቆብ መስዋዕትን እንደሰዋ እናነባለን:: ለምንድነው ከቤቱ ሲወጣ መስዋዕቱን ሰውቶ ያልወጣው? በሌላ አነጋገር ቤርሳቤህ እስኪደርስ ድረስ መቆየት ለምን አስፈለገው?
3. በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ለያዕቆብ አንዳች ነገር ከመናገሩ በፊት ያደረገው ነገር ምን ነበረ? ይህንን ያደረገበት ምክንያት ለምንድነው ትላለህ? 1ኛ ሳሙ 3:4-11 ትን ማንበብ ሃሳብ ለማግኘት ይረዳል::
4. ዘፍ 12:10-20 እና 26:1-6 ስትመለከት ያዕቆብ ወደ ግብጽ ለመውረድ ሊፈራ ከሚችልባቸው ምክንያቶች አንዱ ምን ሊሆን እንደሚችል ትገምታለህ? ለምን?
5. ያዕቆብ በዚህ ክፍል ውስጥ (ቁ1-4) ከእግዚአብሄር የተቀበላቸውን የተስፋ ቃሎች በመዘርዘር ተናገር::
6. ዮሴፍ ለቤተሰቦቹ ስለወሰደውና ስላደረገው ጥንቃቄ ሁሉ በቁ 28-34 የምታያቸውን ነጥቦች በመዘርዘር ተናገር::
7. በዘፍ 45:10 እና 45:18-20 መሰረት ለምንድነው ዮሴፍ ለቤተሰቦቹን በጌሳም በማስፈር ላይ ያተኮረው? ወንድሞቹና ልጆቻቸው በሙሉ የዚህ በረከት ተካፋዮች መሆናቸው ምን ትምህርት ይሰጠናል?
8. ብዙ የስራ ጭነትና የአስተዳደር ሃላፊነት እያለበት ዮሴፍ ቤተሰቦቹ ላሉበት ሁኔታ ክብደት ሰጥቶ በግሉ ክትትል ሲያደርግ እናያለን:: አንተስ ዛሬ ቤተሰቦችህ ለሚገኙበት ሁኔታ ምን ያህል ትኩረት ሰጥተህ ትከታተላለህ? 1ኛ ጢሞ 5:8

# ጥናት አስራ አንድ (ዘፍ 47:1-31)

የጥናት ዓላማ:- ቤተሰቦቻችን በምንም ዓይነት የኑሮ ደረጃ ላይ ቢሆኑ የምናፍርባቸው ሳይሆን የምንኮራባቸው ሊሆኑ እንደሚገባን ለመማር::
የምናሰላስለው ጥቅስ: «...ከወንድሞቹም መካከል አምስቱን መርጦ፣ ፈርዖን ፊት አቀረባቸው» ዘፍ 47:2

1. በፈርዖንና በዮሴፍ ዘመዶች መካከል የተካሄደውን ውይይት በራስህ አማርኛ ተናገር::
2. ምንም እንኳን በግብጻውያን ዓይን ጸያፍ ሆነው ቢታዩ ፈርዖን ለዮሴፍ ቤተሰቦች ከሁሉ የበለጠውን ምድር ሲሰጥና የስራ ዕድልንም ሲከፍትላቸው ይታያል:: ይህ የሆነበት ምክንት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? ቁ 7-8 (አምላካቸው በፊቱ ሞገስ ስለሆናቸው ነው::)
3. ዕብ 7:7 «ትንሹ በትልቁ እንደሚባረክ ጥርጥር የለውም» ይላል:: በዚህ ክፍል ደግሞ ያዕቆብ ፈርዖንን ሲባርክ እናነባለን:: ታዲያ ፈርዖን በክብሩ የበለጠ ሆኖ ሳለ ያዕቆብን ሊባርክ ሲገባ እንዴት ያዕቆብ እርሱን ሊባርክ ይችላል? (በዚህ ክፍል እግዚአብሄር እንደሚያይ እንጂ ሰው እንደሚያይ አይደለም::)
4. ዘፍ 12:2-3 ያለው ለአብርሃም የተገባለት ቃል እንዴት ነው በከፊልም ቢሆን በቁ 7-10 ውስጥ ሲፈፀም የምናየው?
5. የዮሴፍ ወንድሞችም ዮሴፍ ለሌሎቹ ቤተሰቦቹ ካደረገው ማንኛቸውም ነገር አልጎደለባቸውም:: ከዚህ ለራሳችን ልንቀስም የሚገባን እውነት ምንድነው?
6. ዮሴፍ የተማረና የተከበረ ሰው ሆኖ ሳለ ቤተሰቦቹ በሚገኙበት ዝቅተኛ ደረጃ እንደማያፍር የሚያስገነዝበን የትኛው ክፍል ነው? በፈርዖን ፊት ይዟቸው መቅረቡ ምን ያመለክተናል?
7. ከቁ 13 ጀምሮ ባለው ክፍል እንደምንመለከተው የተራበ ሰው ሁሉ ወደ ዮሴፍ መምጣት ነበረበት:: ዮሴፍን ከዚህ አንጻር የኢየሱስ ምሳሌ ተደርጎ ሊታይ የሚያስችለው ሃሳብ ምን እንደሆነ ግለጽ::
8. በቁ 13-26 ላይ ስናነብ ዮሴፍ ለህዝቡ ምግብን በነጻ ሲሰጥ አንመለከትም:: እህል አሰጣጡን በተመለከተ ዮሴፍ በህዝቡ ላይ የማያስፈልግ ጫና እንዳደረገ ታስባለህ ወይ? በተሻለ መንገድ ሊያደርገው ይችል ነበረ ብለህ የምታስበውን ተናገር::
9. እግዚአብሄር ለያዕቆብ በም 45:3-4 ውስጥ የገባለት ቃልኪዳንና በ47:27-31 ላይ የተጻፈውን ሃሳብ በማነጻጸር የምታየውን እውነት ለወገኖች ተናገር::
10. ሰው በቤተሰቦቹ እንዲያፍር ሊያደርጉት ከሚችሉት ነገሮች ጥቂቶቹን ዘርዝር:: ስለቤተሰብህ ያለህን አመለካከት ከዮሴፍ ጋራ በማነጻጸር በሳምንቱ ውስጥ ራስህን መርምር::

# ጥናት አስራ ሁለት (ዘፍ 48:1-22)

የጥናት ዓላማ፡- ልጆቻችን ከእኛ ሊወርሱት የሚገባቸው ዋነኛው ነገር የዚህ ዓለም ሃብትና ብልጽግና ሳይሆን ሰማያዊ ነገር እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ: «በአባቶቼ በአብርሃምና በይስሃቅ ስም ይጠሩ፤ በምድር ላይ እጅግ ይብዙ፡፡» ዘፍ 48:16

1. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተካሄደውን ድራማ መሰል ታሪክ በራስህ አማርኛ ለወገኖች ተናገር፡፡
2. ያዕቆብ በቁ 15-16 ላይ እግዚአብሄር እረኛ እንደሆነውና ከጉዳትም እንደታደገው ይናገራል፡፡ በያዕቆብ ህይወት እነዚህ ነገሮች ሲፈጸሙ መቼ አይተሃል?
3. በቁ 6 ላይ ስለ ርስት ድልድል ሲናገርና እንዲሁም በቁ 21 ላይ ደግሞ ወደ ከነአን ስለመመለሳቸው ከሚናገራቸው ንግግሮቹ ስለ ያዕቆብ ምን ትማራለህ?
4. 1ኛ ዜና 5:1 ና ዘፍ 48:5-6 ትን በማንበብ የምትረዳውን እውነት ተናገር፡፡ (ዮሴፍ እንደበኩር ልጅ እጥፍ ድርሻ እንዳገኘ በሁለቱ ልጆቹ በኩል)
5. በቁ 5 እና 6 መሰረት ያዕቆብ ምናሴንና ኤፍሬምን እንደ ልጆቹ ሲቀበል የእስራኤል ነገድ አስራ ሶስት መሆኑ ነው፡፡ ለምንድነው ታዲያ ከነዓን ለአስራ ሁለት ነገዶች ብቻ የተከፋፈለው?
6. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዮሴፍ የእግዚአብሄርን ሃሳብ ሊያይ ያልቻለበት ስፍራ ተናገር፡፡ ከዚህስ ለራስህ የምትማረው እውነት ምንድነው?
7. ዘፍ 48:15-20 ዮሴፍንና ልጆቹን የባረከበት በረከት ከእግዚአብሄር ያገኘው ለመሆኑ ዕብ 11:21 እንዴት ማረጋገጫ ሊሆንልን ይችላል?
8. ያዕቆብ በዚህ ምንባብ ውስጥ ስንመለከተው ለልጁና ለልጅ ልጆቹ እያስተላለፈ ያለው ውርስ ምን ነበረ? አንተስ ለልጆችህ ለማውረስ የተዘጋጀኸው ነገር አለህ ወይ? ከያዕቆብ ጋራ ምን ያህል መመሳሰል አለው?

# ጥናት አስራ ሶስት (ዘፍ 50:1-26)

የጥናት ዓላማ:- ሰው ክርስትያን ስለሆነ ለወዳጆቹ ማልቀስ እንደሌለበት ተደርጎ የሚነገረው ሃሳብ ትክክል ያለመሆኑን እና እንዲሁም ሰዎችን እንዳያለቅሱ መጫን እንደማይገባን መሆኑን ከዮሴፍ ህይወት ለመማር::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «...ድምጻቸውን ክፍ በማድረግ ምርር ብለው አለቀሱ፤ ዮሴፍም በዚያ ለአባቱ ሰባት ቀን ልቅሶ ተቀመጠ::» ዘፍጥረት 50:10

1. በምዕራፍ 50 ውስጥ የተፈጸሙትን ሶስት ዓበይት ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር::
2. በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ዮሴፍ ለሞተው አባቱ ያሳየው ስሜት ምን ይመስል ነበረ? ሌሎቹ ወንድሞቹ ያሳዩትን ስሜት ከዮሴፍ ጋራ ሲነጻጸር ምን ይመስል እንደነበረ አስረዳ::
3. ለምንድነው በዮሴፍና በወንድሞቹ መሃል ለሃዘኑ ያላቸው የስሜት ልዩነት የጎላ መስሎ የሚታየው?
4. ለሚሞቱት ዘመዶቻችን ማሳየት ስለሚገባን የስሜት አይነት ከዚህ ክፍል መማር የምንችለው እውነት አለወይ? ካለስ ምንድነው ትላለህ?
5. በቁ 15-21 ላይ የሚካሄደውን ሁኔታ በራስህ አነጋገር ግለጽ:: ዮሴፍ በዚህ ክፍል ውስጥ ያለቀሰው ለቅሶ በቁ1 ላይ ካለቀሰው ለቅሶ የሚለየው እንዴት ነው?
6. በውሸት ይቅርታን ለማግኘት ሙከራ ሲያደርጉ ይህ ክፍል ያሳየናል:: በተደጋጋሚ ዮሴፍ ለወንድሞቹ ይቅርታ እንዳደረገላቸው ነግሯቸው ሳለ ለምንድነው እነርሱ ይቅርታውን ሙሉ ለሙሉ ለመቀበል የተቸገሩት?
7. «እኔን በእግዚአብሄር ቦታ ማን አስቀመጠኝ?» ቁ 19 ማለቱ ዮሴፍ ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
8. ዮሴፍ ለአባቱ በሞተ ጊዜ ያደረገለት ጥንቃቄና እርሱ ራሱ በሞተ ጊዜ ደግሞ ሌሎች ለእርሱ ያደረጉለት የምታየው ተመሳሳይ ነገር ምንድነው? ከዚህ አኳያ ገላትያ 5:7-10 በምን መንገድ ተፈጻሚነት አግኝቷል ትላለህ?
9. የዘፍጥረትን መጽሐፍ አጀማመርና አጨራረስ በማነፃፀር ስትመለከት የምታየው ነገር ምንድነው? በዘፍጥረት አጨራረስ የእኛ ነገር እንደማይቀጥል የሚቀጥለው መጽሐፍ ተስፋ የሚሆን በምን መንገድ እንደሆነ አስረዳ::
10. ለቅሶ የተቀመጠ አማኝ ሲገጥምህ ማለት የማይገባህ ምን ነገር ለራስህ ተማርክ? በ1ኛ ተሰ 4:13 መሰረት አማኝ የተከለከለው ተስፋ እንደሌለው ሰው ያለ ለመጽናናት እንቢ የሚልበት ደረጃ እንዳይደርስ ስለሆነ ለራስህም ለሌሎችም ይህንን እውነት ተረዳ::